# *ጠላት ምንጊዜም ጠላት ነው*
# *መጠንቀቅ የሚያሻው ከጉያ ወጥቶ*
# *ወደ ጠላት ሰፈር ለመግባት የሚያሰፍሰውን ወስላታን ነው!!*

**ከዝግጅት ክፍላችን**

1. *በሀገራችን ተከስቶ የሚገኘውን የፖለቲካ፤ ማህበራዊና የኤኮኖሚ ቀውስ ለማስወገድና ፍትህ፤ እኩልነት፤ እድገትና ብልጽግና፤ ሰላምና ማህበራዊ መረጋጋት የሚገኝበት የተቻለ ሥርአት ለመገንባት ትግልን የግዴታ ማለቱ የፖለቲካ ሳይንስ አልፋና ኦሜጋ ከመሆኑ ሌላ ሀገር ወዳዶች ሊያልፉት የማይችሉት ሀገራዊ ግዴታቸው ነው ቢባልም አግባብነት ያለው ይሆናል። ይህ ትግል ውስብስብ፤ ከፍተኛ ውጣ ውረድና እልህ አስጨራሽ በመሆኑም ስኬታማ ለማድረግ መስዋዕትነት መክፈልን ጠያቂ መሆኑ በሁሉም ዘንድ ባይሆንም ቢያንስ ለኛ ግልጽ ነው። ሁለቱን ሥርአት በማስወገድ ሶስተኛውንም ደግሞ ወደ ታሪካዊ መቃብሩ እንደአመጣጡ ለመሸኘት የእድሜ ባለጸጋ ሆነውና በትግል ላይ ከሚገኙት አምባ፤ ትግሉም ሆነ መስዋዕት ክፍያው በተግባር እየታዩ ስለመሆናቸው አሌ ሊባል የሚችል አይደለም። ምንም እንኳ በተወሰነ የታሪክ ወቅትና የትግል ሂደት ስውር አላማቸውን በአደባባይና ግልጽ በሆነ ውይይት ተግባራዊ ማድረግ የማይቻላቸው፤ ለማድረግም አቅሙና እውቀቱ የሌላቸው በተለይም ደግሞ የሥልጣን ጥምና ባልሰሩት ተግባር ልታወቅ ባይነት የሚያጠቃቸው ጥቂት ግለሰቦች በአንጃነት ተቧድነው የተወሰነ ጊዜያዊ ችግር ሊፈጥሩ ቢችልም የጀመርነውን ትግል ግን የቀድሞዎቹ ሊያጨናግፉት እንዳላቻሉ ሁሉ የዘንድሮዎችም ሊያኮላሹት ስለማይችሉ፤ በአሸናፊነት እንደምንወጣው ቅንጣት ታህል ብዥታ የለንም። በአሁኑ ጊዜ ከማንኛውም ኢትዮጵያዊ የሚጠበቀው የመለስ አገዛዝ አፋኝ ሥርአትን አስወግዶ በምትኩ ዴሞክራሲያዊ ሥርአትን ለመመስረት በሚደረገው ሁለገብና ሀገራዊ ትግል የየበኩሉን አስተዋጽኦ ማድረግ እንጂ ሌላ ሊሆን አይችልም። ከዚህ በተለየ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ እየታዘብን እንዳለው ለትግሉ ስኬታማ መሆን ባላቸው አቅም መስዋዕት እየከፈሉ ትግል የሚያደርጉትን ድርጅቶችና መሪዎቻቸውን አባላቶቻቸውንም ጭምር ማጥላላትና ተጨባጭ ሁኔታዎችን በማጣመም እየተደረገ ያለው የውንጀላ ተግባር ከተንኮለኝነት የመነጨ አሳፋሪና አፍራሽ ተግባር መሆኑ ከጥርጣሬ የሚገባ አይደለም። ይህ ደግሞ በተጨባጭ ሲታይ ኢትዮጵያን ከወያኔያዊና ከአጋሮቻቸው የጥፋት ተግባርና*

የዘረኞች ተውሳክ ለማላቀቅ እየተደረገ ላለው ትግል በዋና እንቅፋትነት ተፈጥሞ ያለውን የመለስ አሸባሪ አምባገነን አገዛዝ የሚጠቅም መሆኑን የተገነዘቡ ቁጥራቸው ከጊዜ ወደጊዜ እየተበራከተ በመሄድ ላይ ይገኛል። ይህም ያለ ምክንያት አይደለም። ድርጊታቸው ከእርምት ትችት፤ ከገንቢ አስተያየት፤ ለትግሉ ግንባር ቀደም አስተዋጽኦ ከማድረግ ጋር ፈጽሞ የተጣላ በመሆኑ ከመቼውም ጊዜ ግልጽ እየሆነ በመምጣቱ ነው። ውግዘትን፤ ወጊዱልን መባልን እያስከተለባቸው በመሆኑ እርቃነ ስጋቸውን እየቀሩ በመምጣት ላይም መሆናቸው ከየቦታው የሚደርሱን ዜናዎች ያረጋግጣሉ። የሕዝብ ወዳጅ ለመምሰል በተለያዩ መድረኮች እያደረጉ ያሉት ጥራት ውስጣዊ ይዘቱ ከመለስ አገዛዝ ጋር ለመተቃቀፍ የታሰበ እጅ መንሻ መሆኑ ስለተጋለጠባቸው ውርደትን በመከናነብ በቀቢሰ ተስፋነት ውር ውር ሲሉ ይገኛሉ። ፈረንሳዮች ውርደት ከየትኛውም መሳሪያ የበለጠ ይግደላል የሚሉት ያለምክንያት አልነበረም። የጠቆረ ምሽት የቀኑን ውበት ያሳያል እንደሚባለው በነሱ መሰሪ ተንኮል የኢሕአፓን ማንነት፤ ውስጠ ባህሪዩን ጭምር ከመቼውም በበለጠ ለሕዝባቸው ቀናኢ አስተሳሰብ ላላቸው ለብዙሃኑ ግልጽ ሊሆን ችሏል ቢባል ሀቁን መናገር እንጂ ሌላ አይሆንብንም። እነዚህ ሀገር ወዳድ የሆኑ ማህበርሰብ ክፍሎች የመለስ አገዛዝን ለማስወገድ የሚደረገው ትግል ጥንካሬና ስኬታማ ይሆን ዘንዳም መልካም የሆነ ምክራቸውን ለግሰዋል። ከቀና ድርጅቶች ጉያ ወጥተው ትግሉን ለማሰናከል የሚጥሩትን ክፍሎች እንዳመጣጣቸው ቸል ሳይባሉ በቁርጠኛነት በመታገል አገዛዙን ለማስወገድ ግን የሀገር ወዳዱና በሕዝቦቿ እኩልነት ላይ የተመሰረተ በኢትዮጵያ ሀገራዊ አንድነት ላይ የሚያምኑ ታጋዮችን ለማስተባበር የራስን እንቅስቃሴ በማያደናቅፍ መልኩ የተጀመሩትን ጥረት አሁንም እንደቀድሞው በከፍተኛ ደረጃ እንዲቀጠልበት እያሳሰቡ ይገኛሉ። ይህንን ሀላፊነት የተሞላበት ጥሪ ማድረጋቸው የሚደገፍ ነውና በሱ ዙሪያ የሚነሱትን አንዳንድ ነጥቦችን ማንሳቱና ግልጽ ማድረጉ ተገቢነት ያለው ነውና እነሆ እንላለን።

2. ባለፉት ጊዜያት ለመገንዘብ እንደተቻለው ከተግባር ይልቅ ማውራቱ ጎልቶ በመገኘቱ “ተባበሩ ወይንም ደግሞ ተሰባበሩ” የሚለው መፈክር ለሰሚ ጆሮ እስኪሰለች ድረስ ለመነገር ምክንያት ሆኖ የነበረ መሆኑ የሚታወስ ነው። እንዲያውም ይህንኑ መፈክር በተለይ ከትግሉ ዳር ቆሞ ተመልካች በሆነው ዘንድ እንደተፈለገ የተወረወረ ብቻ ሳይሆን ይሁነን ተብሎ ከመለስ አገዛዝ ባልተናነሰ መልኩ የተወሰኑ የፖለቲካ ቡድኖችን በተለይም ደግሞ የተለየ የትግል ሥልት ያላቸውን ለማጥቃት ስውር መጠቀሚያ ለማድረግ እንደተቻለ የሚታወስ ነው። ምክንያቱ ደግሞ ግልጽ ነበር። እነዚህ የተለየ የትግል ሥልት ያላቸውን ተቃዋሚ ክፍሎች በተለይም ኢሕአፓ ላለፉት አስረተ አመታት ሕዝባችንን አንቀው የያዙትን ችግሮች አመቺ መስሎ በታያቸውና ትግሉ በጠየቀውና ግዴታ ባለበት ለማስወገድ የራሳቸውን አስተዋጽኦ

ያበረከቱና እያበረከቱ ያሉ፤ ብዙ የታገሉና ከፍተኛ መስዋዕትነትም የከፈሉ፤ በዚህም ተሰፋ ባለመቁረጥ አሁንም እየተንቀሳቀሱ ያሉ በአርአያነታቸውም ሆነ በሕዝብ አለኝታነታቸው አኩሪ ታሪክ ያላቸው በመሆናቸው ነው። በሀገር አንድነትና በኢትዮጵያ ጥቅም ላይ ከቶምና መቼም አልደራደርም የሚለው ኢ.ሕ.አ.ፓ አሁንም በትግሉ አውድማ መገኘት ለብዙዎች አሎሎ እሳት ሆኖባቸው ያለ በመሆኑም ጭምር ነው።

3. የመተባበሩ ጉዳይ ሁሉም በሚመኘው ደረጃ አለመሳካቱ፤ በድርጅቶች መካከል ያለው ንትርክ መኖሩ ወይንም ደግሞ መከፋፈልም ሆነ አንጃ መፈጠሩ ብዙውን የሚያሳዝን ቢሆንም ላለመሳካቱ ከአንዳንዶች የሚሰጠው ምክንያት ግን "ከመፈላለግ ይልቅ መጠላለፍ አለ" በሚል ማቅረቡ ስህተት ብቻ ሳይሆን የነገሩን ጭብጥ ለማሳሳት ከሚደረግ ሙከራ ሊያልፍ አይችልም። ትግልን ወደኋላ ጎታች እንጂ ቅንጣት ታክል ወደፊት የሚያራምድ፤ ለሁኔታውም ጥራትና መልካም ግንዛቤ የሚያስገኝ ሊሆን አይችልም። በአሁኑ ወቅት ሕዝብም ሆነ ታጋዩ ክፍል ባለፉት ጊዜያት ከተደረጉት የመተባበር ጥረቶች በርካታ ተመክሮዎችን ቀስሟል ብለን እናምናለን። ማን ለሕዝቡ እንደቆመና ማን ደግሞ በአስመሳይነት እየተንቀሳቀሰ እንዳለ በሚገባ የሚያውቀው ነው። ቀን ተቃዋሚ ሲመሽ ደግሞ ከአገዛዙ ቱባ ቱባ ባለሥልጣናት ጋር አሸሼ ገዳዎ ከሚሉ አስመሳይ ታጋዮችና እንመራዋለን ከሚሉት ቡድን ጋር በምንም አይነት ተአምር የትግል መተማመን ሊፈጠር እንደማይቻል ሳይታለም የተፈታ ነው። እነዚህ ሰልፋቸው ከጠላት ጎን እንጂ በምንም አይነት በተቃዋሚነት ስም ከሕዝቡ ጎን እንዳይደሉ ተግባራቸው በበቂ የመሰከረው ነው። ይህ ተመክሮ ሁሌም ከግንዛቤ መግባቱ ጠቃሚነቱ የጎላ ነው። ስለሆነም አስመሳዩ ከታጋዩ ተለይቶ እንዳይቀመጥ ሁኔታውን ለማድበስበስ ካልተፈለገ በስተቀር በነዚሁ ሁለቱ መካከል ሕብረትና ትብብር ማግኘት እንደማይቻል ግልጽ መሆኑ ከሕዝብ ግንዛቤ ውስጥ ከገባ አመታትን አስቆጥሯል ቢባል ከስህተት የሚጥል አይደለም። የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ሕብረትን ለመመስረት በተደረገው ሂደት በግልጽ የታየ በመሆኑ ምስክር መጥራት የሚያሻ አይሆንም። የመለስ ቡድን "ጠላታችን አይደለም ወይንም ተቃራኒ ሳንሆን የተለየ አቋም ያለን ነን"፤ "ከኢሕአደግ ጠብ የለንም" ተብሎ ሲስተገባ የነበረውና አሁንም በአንጃነት ብቅ ባሉት ክፍሎች አማካኝነት ቀደም ብሎ ውስጥ ውስጡን ተብላልቶና አሁን በግላጭ ሊወጣ እንደቻለው ከወያኔ ለመጠጋት ዳዴ ከሚሉ ጋር ተመልሶ በአንድነት ለመሥራት እንደሚያስቸግር መገንዘቡ አዳጋች አይሆንም። በአንጃኛነት የተከሰቱ ጥቂት ግለሰቦች ስህተታቸውን ተገንዝበው ወደ እናት ድርጅታቸው ተመልሰው እንዲቀላቀሉ ለማስቻል ግፊት የሚያደርግ ማንኛውም ግለሰብም ሆነ ቡድን በተለይም ደግሞ በአስታራቂነት የሚሰማራ በአገዛዙና በደጋፊዎቹ ብሎም በዳዴ ባዮች

ላይ እየቀረበ ያለውን የመረረ ትችትና ብሎም ከሌላው ነጥሎ ለማስቀረት የሚደረገውን ትግል ለማኮላሸት የሚደረግ ስምሪት እንጂ በሌላ በምንም ሊፈረጅ አይችልም። ይህ ደግሞ የኋላ ኋላ ሀገር ወዳዱን በአገዛዙ ለመጥለፍ በመስለቢያነት ሊያገለግል ይችላልና ተቀባይነት ሊኖረው የሚችል አይሆንም። የዚህ አይነት እንቅስቃሴ ሕዝብን ለመረማመጃ ታጋይን ለአጋዥነት ድግስ ማሰናዳት ነው። ለወሳኝ ትግል የሚያነቃቃ ሳይሆን የሚያኮራምት፤ የሚያበረታታ ሳይሆን የሚያዳሽቅና የሚያዘናጋ ነው። ከብት እንጂ ታጋይ የሆነ የሰው ፍጡር ከአራጁ ጋር እንዲውል መሞከር ከስህተትም በይቅርታ ሊታለፍ የማይችል ስህተት መሆኑ ባይረሳ መልካም ይሆናል። ኢሕአፓ ለዚህ ዝግጁ የሚሆን ሳይሆን አጥብቆ የሚታገለው መሆኑ በግልጽ ሊታወቅ ይገባል እንላለን።

3. ማንኛውም ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ሕዝባዊነትን እስከተላበሰና በብዙሃኑ ሕዝብ እስከተደገፈ ድረስ ለወቅቱ ተስማሚ የሆነ የትግል ሥልት ይኖረዋል። ማንኛውም ታጋይ ከልቡ ለትግሉ ቆርጦ ከተነሳ የትግል ሥልቱን የመምረጡ ሃላፊነት የግሉና በሚኖረው የርዕዮተ አለምና እይታ ግንዛቤ መሰረት የግድ በሚለው የሚወሰን ሲሆን በዚህ ጥያቄ ላይ እንካ ሰላንቲያ የሚገጥም አይኖርም። የስልቶቹ ትክክለኛነት መፈተኛው የትግሉ አውድማ ነውና የሁሉም ትኩረቱ በዛ ላይ ሊሆን ይገባል። ይህ በንዲህ እንዳለ በግልጽም ሆነ በስውር ከጠላት ጉያ ለመግባት የሚደረግ ሽር ጉድ ተደርጎ አላዋጣ ሲልና ተቀባይነትም እያጣ መሄዱ ተስፋ አስቆርጦ በሌላ በተዘዋዋሪ ለሕብረት ለመታገል ራስን ለማጬት መዳዳቱ የሸሹትን በሌላ መለክ ለማጥፋት ቢያንስ ለማዳከም የሚደረግ የተንኮል ጥረት ነውና ከሀገር ወዳዱ በኩል አስፈላጊው ተቃውሞ የሚገጥመው መሆኑ ሊታወቅ ይገባል። ይህንንም የግል አጀንዳዎቻቸውን ስኬታማ ለማድረግ ለንደዚህ አይነት ክፍሎች ይፋም ሆነ ስውር ድጋፍ የሚያደርጉትን በምንም አይነት በቸልታ የምንመለከታቸው እንዳለሆነ ግልጽ ሊሆን ይገባል። እነዚህ ከዋናው ጠላት ባልተናነሰ ደረጃ በኢሕአፓ ላይ እየዘመቱ ያሉ ክፍሎች ቀደም ብሎ በተመሳሳይ ሁኔታ የተገለሉ አጥፊና ከፋፋይ ግለሰቦች ድጋፍ ማግኘት ተመሳሳይ ላባ ያላቸው አብረው ይበራሉንን ያስታውሰናልና ቀጥሉበት እንላለን።
4. ደጋግመን ለመግለጽ እንደሞክርነው የትግል ሥልትን ለመቀየስ ተጨባጩን ሁኔታ በሚገባ ዘርዝሮ መተንተንን፤ ከጭፍን ጥላቻ በመራቅ ሆኖም ግን ጠላትንና ወዳጅ በቅጡ መለየትን፤ የሃይል አሰላለፍን በሚገባ ማወቅን፤ የሕዝብ እንቅስቃሴዎች ድክመታቸውንና ጥንካሬያቸውን አብጠጥሮ ማወቅን፤ የፖለቲካና የኤኮኖሚ ሥልጣንን በቁጥጥሩ ሥር ያደረገውን ቡድን በተለይም ቀንደኛ ወኪሎቹን ማንነት በሚገባ መረዳትን፤ የትኛው የኤኮኖሚ አውታር በማን እጅ እንዳለ ተከታትሎ ዜና ማግኘትን፤ የታጋዮች

የትግል ቅንብር በምን ደረጃ ላይ እንዳለ መገንዘብን፤ የትግሉ ራዕይ፤ ግብና ኢላማ ማወቅን፤ ለጠላት ክፍት ሆኖ አለመገኘትን፤ ሚስጢርን ለማይመለከታቸው ሁሉ አለማዝረክረክን፤ ከባዕዳን ባለሥልጣናት ጋር የሚደረጉ ግንኙነቶች ከሕዝብ ጀርባ እንዳይሆኑ መታገልን የነሱንም እንቅስቃሴዎቻቸውን በቅጡ መከታተልን፤ የሕዝቡን ታሪክ፤ ባሕሪይ፤ ባሕልና እምነትን፤ ጥቅሙንና ፍላጎቱን በሚገባ ማወቅን ይጠይቃል። በርካታዎች ከስህተት እየወደቁ ያሉትና የኋላ ኋላ በመለስ አገዛዝ መዳፍ ሥር ወድቀው የታሪካ አተላ የሚሆኑት ይህንን የሕብረተሰብ መሰረታዊ ፍላጎትና ምኞት በቅጡ ባለመገንዘባቸው አለበለዚያም እድሜ ሲገፋ አርቆ የማሰብ ችሎታ እየጎደላቸው የተጣመመ አመለካከት ሊይዙ በመቻላቸው መሆኑ ከጥርጣሬ አይገባም።

5. በትግል ስልቶቹ ላይ ልዩነቶች መኖራቸው የሚጠበቅና መከበር የሚገባው ሲሆን ትኩረት መስጠት የሚገባው በስልቶቹ ላይ ሳይሆን በየትኛውም ቢሆን ቆርጠ በመታገሉና ሕዝብን እያደራጁ በማታገሉ ላይ ሊሆን ይገባዋል። ሕዝብ የራሴ መንግሥት የሚለውን እስኪመሰርት ድረስ ትግሉን በየደረጃው እንደሁኔታው ማካሄድ፤ ግብታዊውን ከተቀናበረው ጋር ማቆራኘት፤ የከተማውን ከገጠሩ፤ የአስተማሪውን ከተማሪው፤ የወታደሩን ከሕዝቡ፤ የነጋዴውን ከሸማቹ፤ የፖለቲካውን ከሕዝባዊ ድርጅቶችና ከእቁቦች፤ እድሮችም ሳይቀሩ እያጣመሩ የመለስ አገዛዝን በሚገባ ማስጨነቅ እንጂ የተለየ የትግል ስልት ባላቸው ላይ መሰመራቱ በተጨባጭ ሲታይ ጥቅሙ ለአገዛዙ ብቻ ነው።

6. በስጋት ደረጃ እየተባለ ሆኖም ግን የራስን ድብቅ አላማ ለማስረገጫ እንዲያገለግል እየተቀነቀነ ያለው ሀሳብ በጠመንጃ የሚደረግ ሹም ሽርን የሚመለከት ነው። ሀሳቡ በመመኘት ደረጃ መልካም ቢሆንም በወደፊቷ ኢትዮጵያ ሌላ አዲስ አምባገነን ከሥልጣን መቆናጠጥ አለመቆናጠጥ የሚወሰነው በወቅቱ የትጥቅ ትግል ስለሚካሄድ ሳይሆን የባዕዳን ጣልቃ ገብነት እንዳለ ሆኖ በመሰረቱ ባለው አገዛዝ ጠባይና በሚከተለው ፖሊሲ፤ በሚያከናውናቸው ተግባራት በአንድ በኩል፤ በሌላ በኩል ደግሞ ሕዝቡ መብቱን ለማስከበርና ነጻነቱን ለመጎናጸፍ በሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች የመዳከምና የመጎልበት ድምር ውጤት መሆኑን የሚዘነጋ ነው። ማንም የደህንነትና በሰላም ለመታገል የሚያስችል ዋስትናና የፖለቲካ አየር ለመስጠት የሚችል የመለስ አገዛዝ ተቃዋሚ የሆነ ቡድን ሆነ ግለሰብ ሊኖር ስለማይችል ተወደደም ተጠላ መሳሪያ አንግቦ የሚታገለውን ቡድን ትጥቅህን አውርድና የወያኔን ሕገ አገዛዝ አክብረህ በሰላማዊ መንገድ ታገል ብሎ ለማለት ማንም የሞራል ሃላፊነት የለውም። የሚቀበለው ሊኖር አይችልም።

እርግጥ ነው። የፖለቲካ ሥልጣን የሚፈለገው፤ ጠለቅ ተደርጎም ለሱ ትኩረት የሚሰጠው ሰላማዊና የበለጸገች፤ በዴሞክራሲ ሥርአት የምትተዳደር እንዲት

ኢትዮጵያ እውን ለማድረግ ነው። የትግላችን አላማም በዚህም ተባለ በዚያ በሕዝባዊ ምርጫ የስልጣን ሽግግር ሊኖር የሚችልበትን ሥርአት፤ የሕዝቡ የነጻነትና ሰብአዊ መብቶች ያለገደብ ሊከበሩ የሚችሉበትን ሁኔታ ማመቻቸት ነው። ጠላ ካልተጠጣ አላማውን ስቷል የሚለው የአነጋገር ዘይቤ ይህንን መሰል ሁኔታ ለመግለጽ ነው እንጂ ለሌላ አይደለም። መብትና ግዴታን ማወቅ በአንድ በኩል፤ በሌላ በኩል ለመብት መከበር ቆርጦ መታገልና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም መስዋዕትነት ለመክፈል ዝግጁ መሆን የተለያዩ ናቸውና።

ስለዚህም ሀገር ወዳዱ ቡድን በሚገባ ተደራጅቶ ራሱንም አጠናክሮ ሕዝብ የቀን ተቀን ኑሮዉን እየኖረ መብትና ግዴታውን እንዲያውቅ እየቀሰቀሱ በትግሉ ቀጥተኛ ተሳታፊ እንዲሆን ከፍተኛ ጥረት ካልተደረገ ለአምባገነንነት ምቹ ሁኔታ መፈጠሩ የማይቀር ነው። የዚህን ጊዜም ከሕዝብ ፍላጎትና ጥቅም የተለየ ተልዕኮ ያላቸው ቡድኖች በሰላማዊ ተባለ በመሳሪያ ሀይል ከሥልጣን ለመቆናጠጥ አመቺ ሁኔታ ይፈጠርላቸዋል። የተወሰኑ ምሁራን ተበዬዎች ሕዝብን ለማደራጀት እንቅስቃሴ ሳያደርጉ ሑኡታ ብቻ በማሰማትና ወይንም በማስጠንቀቅ ብቻ ከተወሰኑ የሚፈራው ነገር መከሰቱ አይቀሬ ነው። ለነገሩ ከትግል ውጭ ማንም ቢሆን የሚፈራው የአምባገነንነት ጉዳይ ለወደፊቱ ላለመከሰቱ ወይንም ደግሞ አስተማማኝና ፍትሃዊ ሥርአት ሁሌም ከሰላማዊ ትግል ብቻ ይወለዳል የሚል የማረጋገጫ ዋስትና የሚሰጥ ሊኖር አይችልም። ማንኛውም የቀውስ ሁኔታ መሰረታዊ ለውጥን ያረገዘ ቢሆንም አይጨናገፍም ወይንም ያልተፈለገው አይወለድም ማለት አይደለም። የደርግም ሆነ የወያኔ ከሥልጣን መውጣት የሚያመለክተን አንድ ሀቅ ቢኖር ይህንኑ ነው። ባለፉት ጊዜያት የተደረጉት ጸረ ወያኔው ትግሎችም ድልን ሊቀዳጁ ሲገባቸው በመሃል ተደናቅፈው ዛሬ የተከሰተውን ክስተት ለማየት ተገደናል። የወደፊቱን አማትሮ በማየትና አርቆ አሳቢነትን መሰረት በማድረግ በዚህ ጉዳይ ላይ እሰጥ እገባ መግባቱ ከእንኪያ ሰላንቲያ በስተቀር የሚያመጣው ጥቅም የለም በሚል ዝም እየተባለ እንጂ እንነጋገር ከተባለማ የዚህ ሑኡታ ባለቤቶች ባለፈው የገማ ሥርአት ዋና አቀንቃኝ፤ አለበለዚያም ዋና ተካፋይና አገልጋይ የነበሩ ለመሆናቸው የታሪክ ማህደራቸውን ማገላበጥ ብቻ በቂ ነው። በሌለው ጠባይና ባሕርይ እንዲሁም ፍላጎት በጊዜ ሂደት ወያኔን ዴሞክራት ለማድረግ የተደረጉት ጥረቶች ውጤት አልባ መሆናቸው ባይዘነጋ ለሁሉም መልካም በሆነ ነበር። ስለሆነም በዛው በሰለቸና ውጤት አልባ በሆነ ጎዳና መጓዙ ስህተት ከመሆኑ ሌላ ከሌላው ሙከራዎቻቸው ጋር ሲደመር በተጨባጭ አገዛዙን ማገዝ ስለሆነ አሁንም እንደወትሮው ታረሙ የሚል ምክር በመስጠት ብቻ እንድንወሰን ያለንበት ሁኔታ እንደማይፈቅድልን ቀዩ መስመርን ማለፋቸው የሚያስገነዝበን ነው። አንድ እርምጃ ወደፊት ተኪዶ እንደአመጣጡ መመከት የግድ የሚል ነው። ከዚሁ

ጋርም ተያይዞ የኢትዮጵያ ሕልውና አደጋ ላይ ወድቋል በሚል ማጠየቂያ ከአገዛዙ ጋር ለመቆራኘት ደፋ ቀና እየተባለ የሚስተጋባውና ተግባራዊም ሆኖ ከፍተኛ ጉዳት ያደረሰው መተቃቀፍ ለአገዛዙ ጠቀሜታ አስገኘ እንጂ የሚፈለገው ሰላምም ሆነ የፍትህ ሥርአት ሊወለድ አልቻለም። ከሻዕቢያ ጋር በተደረገው ጦርነት በመቶ ሺ የሚቆጠር ዜጋ ሕይወቱን ቢከፍልም የመለስ አገዛዝ የሥልጣኑን እድሜ ለማራዘም አስቻለው እንጂ መልካም አስተዳደር ሊመሰረት አልተቻለም። ከባድሜ መለስ ወደ መለስ የተባለው የማደናገሪያ መፈክር የውሃ ሽታ ሆነ ቀረ እንጂ ለሕዝብ ጠቀሜታ አልስገኘም። በሶማሌ ከፍተኛ የሕይወት ግብር እያስከፈለ ይገኛል። አሁን እንደሚታየው ደግሞ ሌላ ተጨማሪ ሕይወት ሊያስከፍል ችግሩ አቆብቁቦ ይገኛል።

7. ወያኔዎች ከምንም በላይ የሚፈሩት ስለ ሰላማዊ ሆነ ስለ ትጥቅ ትግል ማውራቱን ሳይሆን በየትኛውም የትግል ሥልት ይሁን እነሱን ቀርጦ የመታገልን ሁኔታ ነው። “ጦርነት መስራት እንችላለን” የሚለው ፉከራና ለሰሚ ጆሮ የሰለቸ የማስፈራሪያ ጩኸታቸው ሥልጣን በጅ ከገባ በኋላ እንዳታፈተልክ የሚደረግ እንጂ መስራቱ ለነሱ ብቻ በስጦታ የታደሉት እውቀት እንዳልሆነ ማንም ያውቀዋል። ሕዝብንም ለመከፋፈል ወያኔዎች ልዩ ተአምር ሰሪዎች ሆነው ሳይሆን ለጊዜው ሕዝባችንን ለንደዚህ አይነት ተግባር አመቺ ሆኖ እንዲገኝ ተለጣፊዎች በረግረግነት መጠመቀሚያ ስለሆኑ ብቻ ነው። ክብርን በነውርነት፤ ሹመትን በቅሌት ማግኘት የሚሹ መድረኩን በማጨናነቃቸው ብቻ ነው።

8. ሀገራችንና ሕዝባችንን የገጠሟቸውን ችግሮች መፍትሄ ለመስጠት በሚል ማጠየቂያ ከወያኔ ጋር ለመጎዳኘት ሰላማዊ ትግልን በብቸኝነት የሚያቀነቅኑት ባብዛኛው በዋቢነት እያስቀመጡ ያሉት ጋንዲን፤ የሰላም ኖቬል ተሸላሚ የሆኑትን ማንዴላን አሁን ደግሞ ውይዘሮ ሳን ሱ ኪ ቢሆንም ይህንን ስልት በልጥጡ ወደ ቀኖናዊነት እየለወጡት ይገናሉ። ፅሁፎቻቸውን ቢጠቃቅሱም ለነሱ በሚስማማቸው ደረጃ እንጂ ለጥራትና ግንዛቤ እንዲገኝ በሚመች መልኩ አይደለም። መደሻ ባለበት ቦታ ሁሉ ነገር ምስማር መስሏቸው ከሆነም ስህተት መሆኑን ማወቅ አስቸጋሪ አይደለምና ቢያስቡበት መልካም ይሆናል።

9. በበኩላችን ሰላማዊ ትግል ሁኔታው አመቺ ሆኖ እስከተገኘ ድረስ ቅድሚያ የሚሰጠውና በሚገባ መጠቀምም አስፈላጊ ሲሆን ሁኔታው አላመች ካለ ደግሞ አማራጭ የትግል ሥልትን መጠቀሙ ተገቢም ሀገራዊ ግዴታ ነው ብለን እናምናለን። ደጋግመን በተለያዩ መጣጥፎቻችን ለመግለጽ እንደሞከርነው ሰላማዊ ትግል በዋናና በመርህ ደረጃ ፖለቲካዊ ይዘት ያለው አመጽ ማለት ነው። እምቢኝ፤ አልገዛም፤ በቃኝ አሻፈረኝ ማለት እንጂ ከአገዛዙ ጋር በመተቃቀፍ በመቻችል እየተበደሉና እየተረገጡ መኖር ማለት አይደለም። የአገዛዙን ሕጎች አላከብርም ብሎ እንቅስቃሴ ማድረግ ነው። የነጋንዲ፤ ሊተር ኪንግ፤ የፖሌስቲና፤ የሶዌቶ እንዳሉ ሆነው ከራሳችን

በ1966 ዓ.ም. ሰኔ 1997 ዓ.ም. ያሳዩን ይህንኑ ነው። የመለስ አገዛዝን ሕግ ተከትሎና አክብሮ ለመብትና ለነጻነት መገኘት ሊካሄድ የሚችል ትግል የለም። ሊኖርም አይችልም። በሕቡዕ መታገል ዛሬም ቀጣይ ሆኖ የተገኘው በዚህ መልክ መንቀሳቀሱ ለትግል ቀና ሆኖ ወይም ተመርጦ ሳይሆን አገዛዙ ሰላማዊ ትግልን ስለማይፈቅድ ብቻ ነው። ሰላማዊ ትግልን ወያኔ እምቢ አለ ተብሎ ደግሞ ትግሉ መቆም ስለሌለበት በማንኛውም መንገድ መቀጠሉ ከአግባብም አግባነት ያለው መሆኑ ቀናኢ ሕዝብ የሚመኘውና የሚደግፈው ነው። የተወሰኑ ጥቂት ግለሰቦች ከኢሕአፓ ጉያ ወጥተው ወያኔን ወያኔ ማለት ስላልፈለጉ፤ የሚያወግዙበት አንጀትም በማጣታቸውና በየቦታው እየዞሩ የአዞ እንባ እያፈሰሱ ከመለስ አገዛዝ ለመተቃቀፍ ወይንም ተቻችለው ለመኖር ሲሉ ለዘመናዊ የትግል እሳት አጥፊነት ራሳቸውን ስለዳረጉ ይፋ ወጥተን በተራና ደም በጠማቸው የወያኔ ካድሬ እንደ ቆሎ እንድንታፈስ የምንፈልግ አለመሆናችንን አለማወቃቸው ከስህተት ቢጥላቸው ተጠያቂ የሚሆኑት ራሳቸው እንጂ ሌላ ማንም ከቶ ሊሆን አይችልም። ወያኔን በእምቢተኛነቱ፤ ሰላምን አሻፈረኝ ማለቱን ሊያወግዙት፤ ወያኔን ወያኔ ሊሉት አለመፈለጋቸው ምስጢሩ ይኸው እንጂ ሌላ አይደለም። የደቡብ አፍሪካ የሰላም ኖቤል ተሸላሚ የሆኑት ማንዴላ ወደ ነጻነት የተደረገ ረዥም ጉዞ በተሰኘ መጽሃፋቸው "በ 1969ን ዓ.ም. የሰላም ትግሉ ቀናት አከተመ። ወደ ትጥቅ ትግሉ ከመሰማራት ሌላ ምንም ምርጫ አልነበረንም"" በማለት በገለጹበት ወቅት በማጠየቂያነትም የተጠቀሙት "የጨካ እንስሳ ሊያጠቃ ሲነሳ በባዶ እጅ ራስን መከላከል አይቻልም" የሚለውን የአፍሪካ የአነጋገር ዘይቤን ነበር። ይህንን ሃሳባቸውን ከትግል አጋሮቻቸው ከሆኑት ውስጥ አንዳንዶቹ "የሰላማዊ ትግል የማይናወጽ መርህ እንጂ ጥቅም የለሽ ሲሆን እንደተፈለገ የሚተው በታክቲክ ደረጃ የሚታይ አይደለም" በማለት ተቃውሟቸውን ባቀረቡበት ወቅት የመለሱት "የኔ ሃሳብ በተቃራኒው ነው። ሰላማዊ ትግል ወደፊት የማያስኬድ ሆኖ ሲገኝ የሚተው ታክቲክ ነበር። ሕዝባችንን ምንም አይነት አማራጭ ሳናቀርብለት ለመንግሥት የመሳሪያ ጥቃት ማጋለጡ ስህተትና ወንጀልም ነው" የሚል ነበር። በዚህ መልክ ማንዴላ የገጠማቸውን ተቃውሞ በወቅቱ ሊያለዝቡ ችለው ነበር። ማንዴላ ግን ቀኖናዊና ግትር ስላልነበሩ ሁኔታው ለሰላማዊ ትግል አመቺ ሆኖ ሲገኝ ትግላቸውን በሰላማዊ መንገድ ቀጥለው ድርጅታቸው ለሥልጣን ሊበቃ ቻለ። ሕዝባቸውም የፖለቲካ ነጻነቱን ሊጎናጸፍ በቃ። ሥልጣን ከጨበጡ በኋላ ደግሞ በሜይ 7 ቀን 2000 ዓ.ም. በአሶሲየትድ ፕሬስ እንደተገለጸው ሕጻናቶች ሲራቡ በሙስና የተበከሉና ብዙ ሀብት ያካበቱ መንግሥታቶችን ለማስወገድ መሳሪያ እንዲያነሱ ጠይቀው እንደነበርም ሊጠቀስ ይችላል።

10. ማንዴላ የተናገሩትን በማንዴላነቱ እናስቀምጠውና ወደኛዎቹ ስንመለስ ግን በሰላሙ የትግል ስልት መደረግ የሚገባውን ማድረግ ሳይሆን የተለየ በአማራጭነትና በአጋዥነት የሚቀርበውን መኮነን ነው የተያያዙት።

እንዳደቼማ ከአፋኝ ሥርአት ወኪሎች ጋር ግብግብ ከመግጠም ይልቅ የእማሬ ጣታቸውን ያነጣጠሩት ለሕዝባችን እኩልነትና መብት መገኘት በሚታገሉት ላይ ነው። የመለስ አገዛዝን አጥብቆ በመታገል ፈንታ እሱን የሚታገሉትን ሀገር ወዳዶችን በዘመናዊ ፖለቲካ በሚል አፍ ማሟሻ መዝለፍ እንደ ከፍተኛ ሞያ ተያይዘውታል። በግልጽም ሆነ በስውር ማስተላለፍ የሚፈልጉት መልዕክት ጠቅለል ብሎ ሲቀርብ ሀገር ወዳዱን ታጋይ ከመለስ አገዛዝ ቱባ ቱባ ባለሥልጣናት ጋር በወረቀትና በቃላት ጋጋታ እየተጎነታተሉ መኖርን እንደ ትግል አድርጎ እንዲወስድ፤ እሱ በቀደደላቸው ቦይ ብቻ እንዲሟልሉላቸው ነው። ይህ ደግሞ በፍጹም ተቀባይነት ሊኖረው የሚችል እንዳልሆነ እነሱም ያጡታል ብሎ ማሰብ የሚቻለን አይደለም። አይ ካሉና በሚያስቡት ጎዳና ከቀጠሉ የታረደች በግ እስክትሞት ድረስ ትንፈራገጣለች ነውና ነገሩ መንገዱንም ሆነ ስለቱን ማቅረቡ የሚገደን እንዳልሆነ ግን ሊያውቁት ይገባል እንላለን።

11. ለማንኛውም ጠላት ምን ቢደልሉት ወዳጅ አይሆንምና እስቲ የሚከተሉትን ጥያቄዎች እናቅርብና የዛሬ መጣጥፋችንን በዚሁ እንቋጨው።

ሀ. የኢትዮጵያ ሕዝብ ከምንም በላይ ከበሬታና ከፍተኛ ዋጋ የሚሰጣቸውን የተፈጥሮ ነጻነትና ሰብአዊ መብት በማን አህሎኝነት እየረገጠና በሕዝብ ላይ በደል የሚያደርስ የመለስ አገዛዝ በጠላትነት ካልተመደበ በምን ሊፈረጅ ይችላል? የሱ አጫፋሪዎችንስ ከየት ጎራ መመደብ ይቻላል?

ለ. በእብሪታቸውና በሕገወጥ ድርጊታቸው፤ በሙስና ተግባራቸው የተጋለጡ የአገዛዙ ከፍተኛ አባላትን በሕግ እንዳይጠየቁ የሚያደርግ አገዛዝ ምን ስያሜ ይሰጠዋል?

ሐ. የሚደርስባቸው እስራት፤ ግድያ፤ ስደትና ጉስቁልና፤ በሰውነት ላይ የሚደረግ እንግልት ሳያስበረግጋቸው ሕዝብ ከድል ጎዳና የሚያደርሰውን ሂደት አብሮ በመምከር፤ ችግርህ ችግሬ፤ ጉዳትህ ጉዳቴ፤ መከፋትህ ክፋቴ፤ ጉስቁልናህ ጉስቁልናዬ፤ ደስታህ ደስታዬ እያሉ በመታገላቸው ከፍተኛ መፈቀርንና መከበርን እንዲሁም ታማኝነትን ያተረፉ ብርቅዬ ዜጎቻችንን በአደባባይ የሚረሽን፤ ደብዛቸውን የሚያጠፋ፤ ገድሎ በተቃዋሚ ተገደለ እያለ አብሮ የውሸት ለቅሶ በሚያለቅስና በሚሳለቅስ በምን ይፈረጃል?

መ. አለአግባብ ዜጋ ከሰራውም ሆነ ከቀዬው የሚያፈናቅል፤ በሀሰትና መሰረተቢስ በሆነ ክስ የሚወነጅልና ለፍርድ አቅርቦ ፍርድ አስጥቶ ዘብጢያ አውርዶ በእስር የሚያንገላታ የፍትህ አልባ ዳኛ በምን ይፈረጃል?

ሰ. ሕዝብን ለጭቆናና ለችግር የሚዳርግ ሥርአተ አልበኛ በምን ሥሙ ይጠራ?

ረ. ለአቤቱታ አፈና፤ ለሰላማዊ ሰልፍ ጥይት፤ ለፖለቲካ ተቃውሞ ፍጅትን በምላሽነት የሚሰጥስ?

ሠ. የኢትዮጵያን ምንነትና ማንነት የካደና ያዋረደ፤ አካሏን ያስገነጠለ፤ ለቀጣይ ግንጠላም ሆን ብሎ በግንባር ቀደምትነት የሚንቀሳቀስ፤ መለያ ባንዲራዋን ጨርቅ ነው በማለት ያንቋሸሸ?

ሸ.. በቀል ባዘለ አመራር የተመረዙ በሕዝብ ጫንቃ ላይ በግዴታ የተቆናጠጡ በሥልጣን ዋልጌነት አድሏዊ አሰራርና ከፋፍይ ድርጊት የሚሰሩ ይሁነኝ ብለውም በተጣመመ አመለካከት ተነስተው ሽብርን የሚያካሂዱ?

ቀ. ሀገርና ሕዝብ እንዲታመስ፤ ልዩነት እንዲነግስ፤ መከፋፈል እንዲፈጠር፤ አንድነት እንዲጠፋ ሌት ተቀን የሚኳትን በምን ይፈረጃል?

በ. ለባዕዳን በሎሌነት በማደር በቅጥረኝነት በመሰለፍ በጎረቤት የውስጥ ጉዳይ በጦር ሀይል ጣልቃ በመግባት ለኢትዮጵያ ሕዝብ ዘላለማዊ እንኳ ባይሆን ለረጅም ጊዜያት የሚሆን ጠላት የሚያፈራ፤ ከነሱ በተቃረነ መልክ ለሕዝቡ የተለየ ሃሳብና ራዕይ ያለውን የመነተሩ፤ በተራበ ሕዝብ የነገዱ፤ በንጹሃን ሕይወት ሕልፈት የከበሩ ይህንን ሲያደርጉም ተሳስተው ሳይሆን ይሁነኝ ብለው የተሰማሩ በምን ይገለጡ? ወዘተ፤ ወዘተ........

ለነዚህና መሰል ጥያቄዎች በሚገባና በማያሻማ መንገድ መልስ ካልተሰጣቸው እንዴትስ ቀርጦ መታግል ይቻላል? ሕዝብንስ በቆራጥነት የሚያታግል ስልትስ እንዴት መንደፍ ይቻላል? በምን መመዘኛ ተለክቶ ነው ካለፉት አገዛዞች ሁሉ የበለጠ ጸረ እኩልነት፤ ጸረ ዴሞክራሲ፤ ጸረ አንድነት ጠባይ ያሳየው የመለስ አገዛዝ መሆኑን መሳት የሚቻለው? የሕዝብን ጠላትና ወዳጅ በሚገባ መለየት ካቃተን፤ የዚህም መንገዱና ዘዴው ከጠፋን እንዴትስ በትግሉ ሂደት ላይ የጠራ አስተያየት ሊኖረን ይችላል? የሀገር ወዳድነት ካባ ለመልበስ የሚፈልግ ለሰላም ጽኑ ፍላጎት ያለው ሁሉ ሰላማዊነቱን የሚያረጋግጠው የመለስን ሕገ አገዛዝ አሜን ብሎ ተቀብሎ ማክበር ሳይሆን ለአገዛዙ አልገዛም አልታዘዝም አሻፈረኝ በማለት በማመጽና አዲስ ሥርአት ለመመስረት እየተጋለ ሕዝብን ሲያታግል ብቻ ነው። ከዚህ ውጭ ሌላው

**ሁሉ ትርፍ ነው። የትም አያስኬድም። ትግል ሲሉ ትግል ይባላልና ሰላም ሲሉ የምንረዳው የምንገነዘበው ለየቅል ነውና እንቅስቃሴያችንም በዘው መቃኘቱ አይቀርምና የግዴታ ልዩነት መከሰቱ አይቀሬ ነው። መፍትሄውም የግዴታ በሕዝባዊ ትግልና በሕዝቡ አሸናፊነት ለመገኘቱ እምነታችን የጸና ነው። ለዚህ ግን ጠላት ወዳጅ ላይሆን መለመኑ ያብቃ እንላለን። ቢመክሩት የማይሰማን፤ ቢለምኑት ለማይራራ ለጨካኝና ጸረ ሕዝብ ሀይል ለመስገድ መሯሯጡ አብቅቶ ለሚመረው፤ ለሚጎመዝዘው ትግል ፊታችንን እናዙር። ያልደፈረሰ አይጠራምና በትግል እስከ ድል ጾንተን እንገኝ እንላለን። እስከዛው ድረስ መልካሙን እንመኝላችኋለን።**